# የኢትዮጵያ ሕዝብ የነጻነት ትግል

# በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አይደናቀፍም!!!

ወያኔ ድፍን 25 ዓመታት ሙሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር ደፍቆ ይዞ ሲያሰቃይ መኖሩን እረስቶ በትናንትናው 29,1,2009 ዕለት ለ 6 ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በማወጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ በብርታት እያደረገ ያለውን ፀረ አንባገነን አገዛዝ የነጻነት ትግልን ለመቋቋምና አሸንፎ እንደገና አስከፊ የአንባገነን አገዛዙን ለማስቀጠል ያለ የሌለ አቅሙን አሟጦ በመጠቀም ሕዝብን ሊፋለም ቆርጦ መነሣቱን አስታውቋል፡፡

ይህ አዋጅ ወያኔ በተለያዩ አዋጆችና ሕግጋት አንዴ "የፀረ ሽብር ሕግ"ሌላ ጊዜ ሌላ አሳሪ ሕግ አሁን ደግሞ "የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ" በማለት ስም እየቀያየረ በአሸባሪ ድንጋጌዎቹ ሕዝብን በማሸበርና በማስፈራራት እጅ እንዲሰጥ አድርጎ አሜን ወዴት ብሎ እንዲገዛለት ለማድረግ ተደጋጋሚ ጥረት ማድረጉን ከማመልከቱ ውጭ ይህ አዋጅ የሚያመጣው ያልነበረ አዲስ ነገር አይኖርም፡፡ 25 ዓመታት ሙሉ ያለ ሕግ ስንተዳደር ወይም ስንገዛ ኖረናልና፡፡

ዜጎች 25 ዓመታት ሙሉ ያለ ፍርድ ይገደሉ፣ ያለ ፍርድቤት ትዕዛዝ ይታፈኑ፣ በነጻ ሐሳብን የመግለጽ መብታቸውን እንዲያጡ ተደርገው፣ የመደራጀት የመሰብሰብ የመቃወም ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ተነጥቀው ይኖሩ እንደነበር፣ ከአሰቃቂ የሰብአዊ መብት አያያዝ ባለፈ በዘር ማጽዳትና ማጥፋት አረመኔያዊ አገዛዝ ስር የቆየን መሆናችን የአደባባይ ምሥጢር ነው፡፡

በመሆኑም ይህ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ከማሸበር ስልትነት ባለፈ የሚጨምርብን አዲስ ቀንበር አይኖርም፡፡

ስለሆነም መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ አዲስ የወያኔ የማሸበሪያ ወሬ ሳንበገር የተያያዝነውን ፀረ የጥፋት ኃይሎች የነጻነት ትግል የጥፋት ኃይሉን የጥፋት እርምጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊቀለብስ በሚያስችል ጥንካሬ በመፋለም የተያያዘውን የሞት ሽረት ትግል በድል ለመወጣት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ተጠናክረን እንነሣ!!!

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!!!

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው
amsalugkidan@gmail.com